# የስንብት ቀለማት ዳሰሳ

ትዕግስት ሳሙኤል

ለኔ የስንብት ቀለማት የሕይወት ቀለማት ነው። አዳም ልክ እንደተዋጣለት የሙዚቃ ኦርኬስትራ መሪ ያቺን ቀጭን ዘንግ ይዞ እያወዛወዘ፣ ከስልሳ በላይ የሆኑ ገጸ ባሕርያትን አስማምቶ፣ የእያንዳንዳቸውን የልብ ትርታ እጅግ በጣም በሚመስጥ የረቀቀ የአተራረክ ስልት ያቀረበልን የሕይወት ቅኝት ነው። ይህ ቅኝት ዜማዉ የሚያምር የፍቅር ቀለማት ነው።
ዜማው የሚያስለቅስ የምቀኝነት፣ የመከዳዳት፣ የሸር፣ የግብዝነት ቀለማት ነው። ይህ ቅኘት ዜማው የሚያባባ፣ የመስዋዕትነት፣ የመረሳት፣ የመጣል፣ የመታመም አልፎም የመሞት ቀለማት ነው። ይህ ቅኝት ዜማው ድንቅ የሆነ የተአምር፣ የተረት፡ የትንግርት፣ የእንቆቅልሽ እና የብርሃን ቀለማት ነው።

መጽሐፉን አንብቤ ስጨርስ ሁለት የጠለቁ ስሜቶች ተሰሙኝ። የመጀሪያው ከልክ ያለፈ መደነቅ ነው። ሁለተኛው ጥልቅ ሃዘን ነው።

ያዘንኩበት ምክንያት በጣም የወደድኳቸው ገጸ-በሕሪያት አጨራረሳቸው ልብ ይሰብራል። ታሪክ አያልቅምና አንዳንዶቹ ገጸ-ባሕሪያት ደሞ እንዲሁ አየር ላይ እንደተንሳፈፉ መዳረሻቸውን የማወቅ እድል ባለማግኘቴ ጉጉቴ አልተቋጨም። 932 ገጽ ሙሉ አንብቤ ጨርሼ «በቃ አለቀ?» ያልኩበት ምክኒያት የአዳም የአጻጻፍ ውበት፣ የአስተሳሰብ ጥልቀት እና የስሜት አኮራኮሩ ከአእምሮ በላይ ስለሆነ መጽሐፉን አንብቤ ስጨርስ አዳም ያለቀብኝ ስለመሰለኝ ነው።

የተደነቅኩበት ምክንያት ደሞ ከ60 በላይ ገጸ-ባሕሪያትን በ932 ገጾች ውስጥ በሚገርም የስምምነት ጥበብ አቀናጅቶ፤ እንስሳ አናግሮ፣ በልጅነት የሰማነውን በጣም ቀለል ያለውን ተረት አግዝፎ፣ መለኮት አልብሶ፤ የእያንዳንዱን ገጸ-ባሕሪ የሕይወት አካሄድ ጸጉር የመቁጠር ያህል በሚመስል ሁናቴ ጥቃቅን ዝርዝሮች ሳይቀሩ ማስፈሩ አስደመመኝ።

አንድ ስዕል የተዋጣለት ማራኪና ውብ ስዕል የሚያደርገው የቀለማት አገባቡ በሚስማማ መልኩ ሲዋሃድ ነው። አዳም ሕይወታቸው በጣም የተለያዩ ገጸ-ባሕሪያትን በቦታ፣ በቁሳቁስ እና በክስተቶችአስተሳሰር (The character's interconnectedness)፣ እያንዳንዱ ገጸ-ባሕሪ ላይ ባውዛ አብርቶ የራሳቸውን የግል እይታ እንዲተነትኑ በመፍቀድ ( Through multiple perspective)፣ ግድፈታቸውን፤ ስኬታቸውን፣ ደስታቸውን፣ ሃዘናቸውን፣ የመንፈስ በሽታቸውን፣ ትዝታቸውን፣ ግብዝነታቸውን እና ጸጸታቸውን ውበት በተሞላበት የአጻጻፍ ስልቱ beautifully intricate የሆነ የስነ-ጽሑፍ abstract painting አቅርቦልናል።

እንደ አንባቢ የኔ ስራ ደሞ እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያገኘሁትን ውበት ለሌሎች አንባቢዎች ማጋራት ነው። My reflection is from the story telling point of view ….፣ የአገላለጽ ውበትን እንደ አዳም የተካነ አለ?
እዚህ መጽሐፍ ላይ ያሉት ሁሉም ገጸ-ባሕሪት የየራሳቸው ስሜት የሚኮረኩር ተሞክሮ አላቸው። ውይይቴን የምጀምረው በጣም ከወደድኩትና አንጀቴን ከበላኝ ጉተማ ከተባለው ገጸ-ባሕሪ ነው።

ለምን ሳበኝ? ጉተማ ማነው? ለምንስ ራሱን ገደለ?

▪ ጉተማ ማህበረሰቡ በትብብር ያደቆሰው ከሚኖርበት ሰሜን ሸዋ ፍቼ ከተማ ለዘመቻ ሀገር አድን ተብሎ ወደ ሐረር የሲያድባሬን ወረራ እንዲመልስ ሚሊሺያ ሆኖ የተጫነ የበግ ነጋዴ ነው። ገጽ 629

(He was a victim of collective violence that was committed indirectly through neglect and systematic injustices. When a society fails to honor or care for someone who has contributed greatly and when they allow that person to suffer and die we can not say he killed himself rather the society that he served faithfully, collectively killed him).

▪ ስለ ሚስቱ ስለዘነበች ሲያወራ፣ ሚስቱን ዘነበችን ያገባት ከሌላ ወንድ አንዷት ሴት ልጅ ወልዳ ነው:: አራት አመቶች አብረው ኖረው አልወለደችለትም፡፡ እሷ ወላድ መሆንዋን ስታስመሰክር እሱ ግን አልሆነለትም። በአጭሩ ጉተማ መሃን ነበር። ገጽ 630. መሃን መሆኑ ግን ያልወለደውን ልጅ ኮትኩቶ ከማሳደግ አላገደውም።

ጉተማ ደግ ነው። ሚስቱን እና የእንጀራ ልጁን ከልቡ ይወድ ነበር።

"ዛሬ በአቧራ ተሸፍኜ ከከሐዲ እጆቻችሁ እርጥባን (የጠብታው ብዛት!) ስለምን በአእምሮዬ ዘነቡ አለች፡፡ የምናፍቅ አይመስላችሁም? ሁለት ባለ ሰንበር ብርድ ልብስ ደራርበን ያሞቀችኝን? ቆዳዬ አንጎል አለው ሙቀትዋን የሚያስታውስበት፣ አፍንጫዬም የማይረሳበት ህሊና አለው ትራስዋ ስር የምታስቀምጠውን በአናቷ ክብደት የተጠፈጠፈ ጠጅሳርዋን የማገው፡፡ በሌሊት እንድነሳ ስትቀሰቅሰኝ፡ የእኔ ጌታ ሊነጋ ነው፣ ጉትዬ ነጋብህ መሰለኝ ጆሮዬም አንጎል አለው የሰማት፣ ጎኔም አይረሳም የዳሳጠችው:: ማኛ የመሰለ የንጋት ሰማይ እያየሁ ለስላሳ ሙቀትዋን ጥዬ የሄድኩበትን ጠዋት.........ጊዮርጊስን ዐይኔ አንጎል አለው የሚያስታውስበት፡፡ መራቀቄ አይደለም፡፡" ገጽ 631

▪ የእንጀራ ልጁ ንጋት ከካሃዲ ፍቅረኛዋ ሚኒሊክ ዲቃላ አርግዛ ቤቱ ተቀምጣ ስትወልድ ጉተማ አላባረራትም እነዲያዉም ያለውን ነዉ ያካፈላት። እንዲህ ነበር የ ጉተማ ደግነት። ትዉልድን ማውደም ሳይሆን ትውልድን መገንባት ነበር የሚወደው። የእንጀራ ልጁ ንጋት ሰለ እንጀራ አባቷ ጉተማ የተናገረችዉን ስናነብ ማንነቱን ለመረዳት በጣም ቀላል ነዉ።
“እንጀራ አባቴ ጉተማ፣ ለእማማ ‘ልጅሽ ወንድ ልጅ አመጣችልኝ’ ያለው ትዝ ይለኛል፡፡ እሱ አልከፋውም፡፡ ዓይኖቹን ለማየት ብፈራም ቀና ብዬ በፈገግታ አየሁት፡፡ ገና አራስ ቤት እያለሁ ሚሊሺያ ሲመለመል በጎቹን ሸጦ ታጠቅ ጦር ሠፈር ገባ፡፡ የሸጠበትን ከግማሽ በላይ የሚሆን ገንዘብ ለልጅሽ ማሳደጊያ ብሎ ትቶልኝ ነው የሄደው፡፡ እነዚህ የሚቀርቡኝ ቢያፅናኑኝም ሃዘኔን ልረታው አልቻልኩም፡፡" ገጽ 535

**ማህረሰባዊ_ጫና (አንድ)**

▪ *መሃን መሆን እንዴት ነው እነደ ድክመት የሚቆጠረው? ጉተማ እግዚአብሄርን በሚያመልክ ማህበረሰብ ውስጥ እየኖረ ማህበረሰቡ አፈጣጠርህ ላይ ድክመት አለ ሲሉት በተዘዋዋሪ እግዚያብሔራቸው ላይ መጠቋቆም አየደለም ወይ? አንድ ግለሰብ ተፈጥሮ የጫነችበትን፣ ከአቅሙ በላይ የሆነን ነገር በሽሙጥና በሃሜት እንዲቀይር መገፋፋት ግለሰቡን ወደ አልተፈለገ የስነ-ልቦና ቀውስ እና ወደ ጥልቅ ሃዘን ይመራል።*

“የመሃንነት ድክመቴን በጨዋታ መሃል እያነሱ በነገር የሚወጉኝ የሚያሸሙዋጥጡኝ አልጠፉም፡፡ በደንብ አስገባ እንጂ ደጃፍ ላይ እያደረክ ነው? የሰዎቹ ተረብ ጨዋታ ነው ቢባልም፣ ጨዋታ ቢሆንም፣ ውስጤ ድረስ ሀዘን ያምሰኛል፡፡ የምተዳደርበት የበግ ንግድ ወንድነትን ይሁን ሀገር ወዳድነትን የሚለካ አልነበረም፡፡ ከወላድ ሴት ጋር አብሬ መኖርና የራሴን መሃንነት መቀበል አልፈለኩም፡፡ ለዘመቻ ገበሬዎች ሲመለመሉ፣ እኔም በጎቼን በርካሽ ጥዬ በወዶ ዘማችነት መጀመሪያ ታጠቅ ገባሁ፣ ከዚያ ሰልጥኜ ሐረር ወረድኩ፡፡ ንግዱ፣ ትዳሩ ያልወለድኩዋትን ልጅ ማሳደጉ፣ ምኑም ተደራርቦ ፍቼን ትቼ ወጣሁ፡፡ ጥልቅ ውትድርና አልተማርኩም፤ ግን ከተጓዥ ነጋዴነቴ ያገኘሁትን በደመ ነፍሴ የተሰገሰገውን የመልካምድር እውቀቴን ስራ ላይ በማዋል በጀልዴሳ፣ በጭናግሰን፣ በጉርሱም የጀብድ ስራ ሰራሁ:: ይሄንንም ልሸለምበት እንጂ ወዳጆቼ መሃል ይሄው አላህ ምስክሬ ነው፣ ታሪክ አድርጌ አንስቼው አላውቅም፡፡ አጠገቤ የረገፉትን በልተው ያልጠገቡ፣ አግብተው እንደ እኔ ትዳር ያልፈተሹ፣ አለንጋ የመሳሰሉ ወጣት ገበሬዎች ሲረግፉ እኔ በመዳኔ የሆነ ወንጀለኛነት ይሰማኛል፡፡ ስንቶች መሰናበቻ አፍታ ሳያገኙ አለፉ? ደህና ሁኑ ለነፍሴ ፀልዩልኝ ብሎ ወዳጅን ለምኖ ማለፍ እኮ መታደል ነበር፡፡ ሻምበል መባሌ አሁን ድረስ ቁስሌ ነው፡፡" ገጽ 631

"ያልሞትኩት ፈሪ ስለሆንኩ ይመስለኛል፡፡ ፈሪ አልነበርኩም፤ ግን ይመስለኛል፡፡ ይቺ አገሬን፣ ያቺ በሚስቴና በእንጀራ ልጄ የተካሁዋት የቀረችኝ አገሬን እሞትላታለሁ ስል እውነቴን ነበር፡፡ የቆምኩት እስዋ ላይ አይደለ፡፡ የምተነፍሰው እሷ ላይ ቆሜ አይደለ፡፡ አቅም የላትም ግን እንደ ዶሮ ጭራ አብልታ ታሳድረኛለች፡፡ ግራና ቀኝ በጠላት ተከባ፣ እንደ ልጅ መከራዋን እንዳላይ አድርጋ ከልላ ጠራም ደፈረሰም ጠላዋን አጠጥታኛለች፡፡ ከሞቀ ቤቴ ወጥቼ፣ ከዘነቡ የሚመች ክንድ የሚሞቅ ገላዋ ተለይቼ ታጠቅ ለስልጠና ስገባ የተኛሁት ፍራሽ ላይ ሳይሆን ደረቅ መሬት ላይ ብርድልብስ አንጥፌ ነበር፡፡ ይሄም የሆነው ደርግ ሊያታልለኝ ፈልጎ አይደለም፡፡ የአገሬ ኪስ እንደዛ ነው።" ገጽ 631

**ማህበረሰባዊ_ጫና (ሁለት)**

"ጀግኖች አምባ ሲፈርስ ጓዶቼ በጋሪያቸው፣ በክራንቻቸውና በወላንሳቸው ለባለሥልጣን አቤት ሊሉ አዲስአባ ሲመጡ፣ ነገር በመጠኑ ተረድቼአለሁና እዚህ መንገድ ገባሁ:: የማላውቀው ሀገር:: ካሸነፈኝ ወያኔና ሻቢያ ምህረት አገኛለሁ? ጅላዋት ሆይ፣ ጮማ ክፋት ከመጣ ሰላሳ እግዚአብሄር፣ ሰላሳ አላህ አይመልሰውም:: ወታደር ስለሆንኩ በተለያየ መልክ እኔንም ደርቦ ልዩ ጥቅም እንዳገኘሁ ሁሉ የወታደር መንግሥት እያለ ሲሳደብ የነበረ ሲቪል ለእኔ ግድ ይሰጠዋል? ሲሰድበኝ ኖሮ ኖሮ እንደገና ሲጨንቀው ትታችሁ መጥታችሁ፣ አገራችንን አስወሰዳችሁ እያለ ከሚያወራ ቀባጣሪው ብዙ ይጠበቃል? ዩኒፎርሜን አውልቄ ጥዬ የማልረዳውን እስከዛሬ የከበደኝን ቀፈፋ ጀመርኩ:: በቀፈፋ ነው የምተዳደረው:: እና ሲያድባሬን ለመመከት ላውንቸር ተሸክሜ በኩራት የተራመድኩበት ጎዳና ላይ፣ ሀገር እንዳሌለው ሰው አፈር እፍ ብዬ ተኛሁ:: ያን የምኮራበትን ዩኒፎርም በዳሙሬ ለወጥኩ:: እግዜር እግሬን በሰበረው ያሉት ይሄኔ ነበር? ተረት መወለጃ መወለጃ አለው እኮ:: ሰበቡ::" ገጽ 632

▪ ከዛ ሁሉ መስዋዕትነት በኋላ፤ ጦርነቱ ካበቃ በኋላ ማህበረሰቡ ጉተማን የናቀበት መንገድ እጅግ አሳዛኝ ነበር። በመጦርያው እና በመከበሪያው ጊዜ በየሆቴሉ የትርፍራፊ ለማኝ፣ የጎዳና ተዳዳሪ መሆኑ አና መናቁ ሳያንስ ቅጽል ስሞች ተሰጥተውት (አለቃ፣ ሳጅን፣ ዕብድ፣ ሰበቡ፣ ሽሜ እና ሌላም ሌላም) ይፌዝበት እና በተራ ጠባቂ ይደበደብ ነበር። አሳዳጆቹ የተዋጋለት ማህበረሰብ አባሎች ናቸው። እንዲህም ሆኖ ግን እስከመጨረሻው ሰአት ድረስ የጉተማ ስብዕና ወርቅ ነበር። በረሃብ በሚንደፋደፍበት ሰዓት እንኩአን ሰዎች የበግ ስጋ ያለበት ትርፍራፊ ሲሰጡት ድሮ ይንከባከባቸው በነበሩት የበጎቹ ትውስታ ምክኒያት እንዲህ ያለ ምግብ አይመገብም ነበር። ለሰው እና ለሀገር ብቻ ሳይሆን ላሳደጋቸው እንስሳቶችም እንኳ የጠለቀ ክብር ነበረው።

"በግን መውደድ ብቻ ሳይሆን አውቃታለሁ:: በግን እንዲህ አይቼ ከየትኞቹ ሴቶች እንደተወለደ መንጋ በርብሬ እነግራለሁ:: የበጉን ፊት በእጇ ይገፍ በህልሙ ምን ዐይነት ሳር እንዳለመና የት እንደጋጠ አውቃለሁ:: በጠጥ አንስቼ እሱን ጨብጬና አሽትቼ ምን ያህል ቀን እንደከረመ፣ መቼ እንደተበጠጠ አውቃለሁ:: ከበጊቷ ላት ውዝዋዜ የፈለገችና ያልፈለገች አውቃለሁ:: ስንት ሆታ እንደሚያስደነግጣቸው፣ ስንት ችግ` እንደሚገራቸው አውቃለሁ:: ስንት ዳበሳ እንደሚያስለመልማቸው አውቃለሁ:: ከአካሄዳቸው የዝናብ ዘመን እተነብያለሁ::.....,,...ታዲያ አብሬአቸው ብዙ ስላሳለፍኩ ዛሬ ዛሬ ምንም ለምኖ አዳሪ ብሆን፣ ለጋሽ የቸረኝን የምግብ ፍርፋሪ አይቼና አሽትቼ፣ የበግ ከሆነ አልበላውም:: በረሃብ ብንደፋደፍም አልበላውም:: ልቤንም ቅር ሳይለው ሆዴ በጠኔ እያጉረመረመ፣ የምላቸው መልሱት እግዜር ይስጥልኝ ነው:: በግ እንዳልበላ ተደግሞብኛል እላለሁ:: ግድ አለኝ "ጥጋበኛ" ቢሉኝ? ብለውኛል።" ገጽ 631

▪ ምትክ የተባለችው ገጸ-ባሕሪም ስለዚህ ጉዳይ ይህን ብላለች።

"ሳጅን በንፋስስልክ መንገዶች ላይ ዟሪ፣ ለምኖ-አደር፣ ጢሙ እስከ ደረቱ የወረደ፤ ዓይኖቹ ሊታወሩ የደረሱ የመሰሉ ወይም የታወሩ፣ ከላይ እስከታች ጨርቅ የተጠመጠመበት ከዘራ ተደግፎ በሰባራ እግሩ እየተጎተተ የሚሄድ ሰውዬ ነው:: ሲለምን ፊት ለፊት የተላላፊ መንገድ ላይ እጁን ዘርግቶ ይቆማል:: የተለገሰውን ወደ አንድ ዐይኑ አስጠግቶ ያጠናውና በቀስታ ጉያው ይከታል:: የሚበላ ሲሰጠው ወደ ዐይኑ አስጠግቶ ያየውና ሥጋ ካለበት "የበግ ነው?" ይላል። "አዎ' ካሉት በቀስታ ይመልሳል:: ካልሆነ ምግቡን ኮሮጆው ይከታል:: ተቀምጦ ሲበላ አይቼው አላውቅም:: አፉ ጉያው ይመስለኛል::" ገጽ 105

▪ ሁሉም አንባቢ ከጠቅላላ የመጽሐፉ ጭብጥ ውስጥ በጣም የሚወዳቸው አንቀፆች አሉት። ለእኔ ከዚህ ስር የተጠቀሱት ሁለት አንቀፆች በልቤ ውስጥ የቀሩ ምርጦች ናቸው።

"አገሬን ነክተውብኝ ጮኼ የተነሳሁ ነኝ:: ምርምር አላደረኩም:: ተማርን እንደሚሉት አገሬን በቃላት ነዝንዤ በፉክክርና በምቀኝነት ለጠላት አልሰጠሁም:: ጠላቷ እንዲደፍራት የእናቴን ቀሚስ ወደ ላይ አልሰበሰብኩም:: ደፋሪው የልጆቿን ታሪክ ሰምቶ ሲርበተበት፣ ሊደፍራትም ሲፎክር "አይዞህ ብዬ የሱሪውን አዝራር አልፈታሁለትም:: እኔ የፊት በር ስዘጋ የጀርባ በር ከፍተው ጠላታቸውን አገራቸው እልፍኝ አስገብተው እናታቸው ተከናንባ የተኛችበትን ብሉኮ ገፈው "ይችትልህ እንዳሉት አጅሬዎች አይደለሁም:: ከርሞ ከርሞ መቆየት ደጉ፣ ጠላ እየጠጣሁ እዛ አለማያ ኮሌጅ የሚያማምሩ ለጋ ወጣቶች ሳይ፣ በልቤ ለመሆኑ ለእነሱ እግሬ እንደ ተሰነከለ ዐይኔ እንደጠፋ ሳንባዬ በብርድ እንደታመመ ይገባቸዋል? እላለሁ:: ጎረምሶቹ ተምረው ጨርሰው ልጄን ንጋትን ከመሰሉ ኮረዶች ጋር ሲሄዱ፣ ሀብት አግኝተው ቢራ ተኮልኩለው ሲጠጡ፣ አሁንም ጠላ እየጠጣሁ አይቼአቸዋለሁ:: አንካሳ በመሆኔ በመንሸዋረሬ ኮራሁ:: ምናልባት ዛሬ እዛ ብሄድ "ወደመጣህበት ሂድ' ይሉኝ ይሆን? ከገደል ይጥሉኝ ይሆን? "ምን ዐይነት ገደል?" በሉኝ። ሜዳም ገደል አለው.......ገደል ወንድሜ አጣጣል ነው:: አወ`ራወ`ር:: የመወ`ርወ`ር መንገዱ.........ሰበቡ........

ወታደር ነበርኩና አልፎ አልፎ ከዛ በተረፈልኝ ወንድነት ብቆጣም ዛሬ ዛሬ ግን ግርማ ሞገሴ የለም፡፡ ወሰናቸውን ስጠብቀላቸው አካሌን ባጎድልም፣ ከምንም የማይቆጥሩኝ መአት ናቸው፡፡ ድሮ በቆራጡ ዘመን ሀገር ለማዳን ስንረባረብ፣ ዛሬ ምን የመሰለ የሚያምር ጫማ ለመግዛት ሲሻሙና ሲያብዱ አያለሁ፡፡ እዛም ጥጥና ጎማ ጎማ የሚሸት ጫማቸው ስር ያልታዘነለት ተሸናፊ ነኝና አፈር እየተነፈስኩ፣ አስፋልት እየላስኩ እርመጠመጣለሁ፡፡ ከጫማቸው የረከስኩ ነኝ፡፡ የሚያወሩትን እኔን ማጣጣያ ዐማርኛ ተራ ሰው ሆኜ አዳምጣለሁ፡፡ የጀልዴሳን አወዳይ ጫት በጎልማሳነቴ ከሲያድባሬ መንጋጋ አላቅቄ እነሱ አፍ አስገብቼ ይሄው መርቅነው በፈዘዙ አይኖቻቸው እያዩ ጣል ጣል ያደርጉኛል፡፡ እገረማለሁ? ኸረ አልገረምም፡፡ ክርስቶስን የከዳው አብሮት ቂጣ የቆረሰ እኮ ነው፡፡ ከሰማይ በታች አዲስ ነገር የለም ቢሉ ዕውነት አለው............ሰበቡ...... " ገጽ 635

**ማህበረሰባዊ_ጫና (ሦስት)**

▪ ዕብድን ማን ይቀብራል? ጉተማ ራሱን ለማጥፋት ሲያቅድ ማህበረሰቡ እንደ ቆሻሻ ሊጥለው እነደሚችል ማሰቡ ራሱ የማህረሰቡን የአረሳስ እና የአጣጣል ጥግ ያሳየናል። ሃዘኑ ምን ያህል ጥልቅ ይሆን? ሬሳው እንደ ቆሻሻ እነዳይጣል ለአፍታ ፍቅር ያሳየችውን ብርቱካንን አሰበ። ድንበሩን ከጠበቀለት፣ ከተዋጋለት እና ከቆሰለለት ከዛ ሁሉ ሚሊዮን ሕዝብ መሃል ልትቀብረኝ ትችላለች ብሎ ያሰበው አንድ ሰው ብቻ መገኘቱ ማህበረሰቡ ጉተማን ከሞተ በኋላም ለመደቆሰ ዝግጁ እንደሆነ ያሳያል። "እስከ መቼ ስበሳጭ፣ ሲበርድልኝ፣ ስቃጠል፣ ስቀዘቅዝ ልኖር ነው? ልቤ ሃሞተቢስነቴን ይረግማል፡፡ ምክንያቱም መሞትን እያሰብኩ ነበር፡፡ የሁልጊዜ ስሜቴ ነው:: ለምኖ ከመብላት ለምኖ ከመጠጣት ሕይወቴ ጋር አብሮ በደም ስሮቼ ውስጥ የሚተላለፈው የመሞት ሃሳብ ነው፡፡ ባልናገረውም ከቡቱቶዬ ጋር ደርቤ የለበስኩት፣ ሸሽጌ ጉበቴ ላይ የተነቀስኩት ሃሳብ ነው፡፡ አብሮ አዳሪዬ ነው፡፡ ሚስቴና ውሽማዬ ነው:: መቼም ይሁን ትቼአት ለምሄደው ለዚህች መሬት እንኪ የምላት ስጦታዬ የምታፍርበትን የምታስፈራራበትን ሞት ነው፡፡ እንደማንም እዚህ እንደሚኖር መንገደኛ ሬሳዬ ረጂ ቆሻሻ ቦታ እንዲጣል አልፈልግም፡፡ ክርስቲያን ነኝ፡፡ ሃይማኖት አለኝ፡፡ ከሞትኩ ምኞቴ ብርቱካን ጋ እደጃፍዋ እንዲሆን ነው:: ትናንት ኮሶ ጠጣሁ ዛሬ መረረኝ፣ ወደ ለሚ ልውጣ ብርቱካን ባገኝ፡፡" ገጽ 645

የ ጉተማ አሳዘኝ አሟሟት

የ ጉተማን ሞት የምንሰማው ስንዝሮ ከተባለው ገጸ-ባሕሪ ነው።
"ሰውዬው ቴፑን በቀስታ ሃይቁ ዳር አስቀመጠና እያነከሰ ወደ ውሃው መውረድ ጀመረ።
ልሂድ ካራ ቆሬ ብርቱካን መጋላ!
ለአንቺም ለአገር አልሆንኩ በውሃ ልበ'ላ!
አላህ ይቅር በለኝ፤ ተክልዬ ማሩኝ!" ገጽ 764

"ሊያደርግ ያቀደው ነገር የገባኝ ሃይቁ ውስጥ እየተራመደ እስከ ትከሻው ሲሰምጥ ነው:: ያልገባኝ መስመጡን በአምባሰል ዜማ ማጀቡ ነው:: የንጋት ቀይ ፀሐይ ጨረሯ ሐይቁ ላይ አርፎአል፡ ቀለባቸውን የሚውጡ አሦች የውሃውን ጠለል ይተከትካሉ.........ሐይቁ የእንጆሪ ጭማቂ ይመስላል. –አቁም! ብዬ ጮህኩ

መጣሁ ልከተልሽ! ማንን ነው የሚከተለው ይሄ ዕብድ? –ማንን ነው የምትከተለው?! ሰውዬው የሰማኝ አይመስለኝም፡፡ ቴፑ ይጮሃል፡፡ ሰውዬው ፊቱን ኣላዞረም፡፡ እግሮቼን ይጠዘጥዘኛል፡፡ ብርዱ ከባድ ነው:: ጭቃ ውስጥ ተሰንቅሬ እንዳልቀር ከሃይቁ ደርዝ ደርዝ እየሮጥኩ እየጮህኩ ለመንኩት። አልሰማኝም፡፡ ወደ ውሃው መግባቱን ቀጥሎ ከአይናችን ራቀ፡፡ ከዛ መፈራገጥ ጀመረ፡፡" ገፅ 765

"ሰፈር ውስጥ ያሉ ውሾች በቁርበቴ ድምፅ ተደናግጠው መጮህ ጀምረዋል፡፡ ጠርቶ ከማይታየኝ ቦታ ከወዲያ ከሃይቁ ዳርቻ፣ ጎጆዎች ጭብጦ መስለው ከተሰበሰቡበት፣ ሁለት ሴቶች ከጎጆአቸው ሲወጡ አየሁ፡፡ ጨኸታቸውን አቀለጡት። ሰውዬው መፈራገጡን አላቆመም፡፡ እንዲህ ሲሆን ያዩት ሴቶች ወደ ሰውዬው ለመምጣት የሃይቁን ደርዝ ይዘው ይሮጣሉ፡፡ ጥቂት ወንዶች ተከተሉአቸው፡ የሸገሩ ሰውዬ መፈራገጡን አቁሞ ውሐው ውስጥ ጠፋ፡፡ እነበረበት ቦታ የአየር እንክብሎች አረፋ መስለው ይታያሉ፡፡ ደበሎዬን ቶሎ ጠቅልዬና ኮሮጆዬ ከትቼ ነጪትን "ተከተይኝ" አልኩና የሚመጡት ሰዎች እንዳያዩን ፈቀቅ ብለን አንድ ትልቅ ድንጋይ ጀርባ ተደበቅን፡፡ የሰውዬው ገላ ውሃው ላይ ተንሳፈፈ፡፡ አራት ሰዎች ተከታትለው ሲደርሱ

ያጋጠማቸው ሬሳ ነው፡፡ ሴቶቹ ሃይቁ ዳር ቆመው አናታቸውን ይዘው "አኒ በዴ ይላሉ፡፡ ወንዶቹ ሃይቁ ውስጥ ገብተው ሰውዬውን ጎትተው ካወጡት በሁዋላ ሬሳው ዙርያ ቆመው ማውራት ጀመሩ፡፡" ገጽ 765

▪ ጉተማን ማን ገደለው? ማህበረሰቡ አይደለምን? (This is a story of collective violence) ጉተማ በትብብር ልናለቅስለት የሚገባ በጣም የወደድኩት ገጸ-ባሕሪ ነው።

▪ የእንጀራ ልጁ ንጋትም ማህበረሰባዊ ጫና ከሚያስከትለው የስነ-ልቦና ቀውስ አልተረፈችም። ከልብዋ ካፈቀረችው አብዮተኛው ሚኒሊክ አረገዘች። እርግዝናዋን በሰማ በሦስት ቀኑ ጥሏት ጠፋ። ልጁን ክዶ አገር ሊገነባ።
"ግራ ጎኔ በሚኒሊክ ትዝታ ሲናጥ ቀኝ ጎኔ በልማድ አሉባልታተገርፏል፡፡ ከዛም ሰምቼአለሁ ስሜ በድንገት እንደጠፋቸውሁሉ የትኛዋ ንጋት? ያቺ ዲቃላ የወለደችው?' ብለውሲያመለክቱኝ ታዘብኳቸው:: ስሜ ከሞክሼ እንዳያምታታ የአባቴን ስም መጨመር ይችሉ አልነበር?፡ 'እ....ጉተማ?'፡፡ ግንአላደረጉትም። ይሄም ያስተዛዝባል፡፡ አብዮተኛ የተባልሽ ሁኚ ያልተባልሽ የተባባልሽ ያልተባባልሽ ያስባልሽ ታዝቤሻለሁ:: ብዙዎቻችን ያልገባንና ያልደረስንበት አስገራሚው ነገር የእኛ ሰው አፍ ሆነ ብሎ እርግማን መጥራት መቻሉ ነው:: የእኛ ሰው አፍ ክፋትን ይፈጥራል፤ ከዛ አሉባልታውን መረጃ ያደርገውና በዕውቀት ተጥለቀለቅሁ ይላል፡፡ ከዛ ይኮራኮማል፡፡ ገዳይም ሟችም ጀግና ይባላሉ፡፡ እናስስ ብንል የአገራችን ሰው በኩታው ስር ስንት ዐይነት ማስመሰልና ቅጥፈት ይዞ እንደሚዞር አሳይ ነበር፡፡ ደመወዝ ለእኔ ዲቃላ አይደለም፡፡ የፍቅር ዘፈን ነው፣ ቃጭሉን እያንከለከለ የወጣ፡፡ ባይሰሙ ደንቆሮነታቸው ነበር። ገጽ 535

"የተበለሻሸውም በዚህ መሰለኝ፡፡ እሱ ሆይ ሆይ መሆኑ እኔ አለመሆኔ፡፡ በሆይ ሆይ ዘመን፣ በያዘው ያዘው አብረው ሆይ ሆይ ያዘው ያዘው ካላሉ፣ ያደናቅፋል፡፡ 'ስህተት' ነው አልወጣኝም፡፡ ያደናቅፋል ነው፡፡ በማርገዜ ከዛም ልጅ በመውለዴ ቢያንስ ልጁ ቆሞ እስኪሄድ ማጥባትና ማሳደግ ስለነበረብኝ ለሆይ ሆይ ለሆሆ ያሰበኝ ድርጅት አልነበረም፡፡ ያ በራሱ ያስጨንቃል፡፡ ሳልዳር በማርገዜ ቂል ብቻ ሳልሆን በፍቼ አብሮ አደግ ወዳጆቼየተበላሸሁ ሴት ነበርኩ፡፡ ህብረተሰቡን በስርነቀል መንገድሊለውጡ የተዘጋጁ ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው፣ በአሉባልታ ሞገድ፣ በፊውዳል ስልት እዛው በዛው ተወልጄ ያደኩበት መስክ ላይ ስደተኛ አድርገውኛል፡፡ ለወሬ ካልሆነ ከልባቸው የቀረቡኝ አልነበሩም፡፡ አንዳንዶቹ እንደውም እነሱን ባለመምሰሌ ልዩ ነገር እንዳመለጠኝ ሁሉ ሊያዝኑልኝ ሲዳዳቸው ታዝቤአለሁ፡፡ የእኔ ጭንቀት ያን ጊዜ ማርክስ ኤንግልስ አልነበሩም፡፡ ብዙ ስለ ሕይወት ያላወቀች ሴት አስረግዘን፣ ያንንም ክደን አብዮተኛ መሆን እንችላለን? የልጄ አባት ከድቶኝ ሲሰወር ምኑ አሪፍ ነገር ነው? ከደርግ ቢባጠስ ተባጣሽ ነው ወይስ ብጣሽ የሚያደርገው?" ገጽ 534

▪ የተኮላ ፈስ

Adam's sense of humor is just as brilliant as his writing skills.

የአቶ ደጃዝማች ልጅ **ተኮላ** ማለት ባጭሩ ያለ በቂ መረጃ በጣም የምትወደውን ሚስቱ ጅማወርቅ ሕላዊን ከእጁ ስር የተነጠቀ ፈሳም ነው።

ስለተኮላ ታሪክ (እውነተኛ አባቱ ማን እንደሆኑ፣ ጅግሳ ስለሚባለው ማንነቱን በስተመጨረሻ ስላወቀው ወንድሙ እና በዱርይነቱ ጊዜ ላስታ ከምትባል ቆንጆ ጋር ተኝቶ ተስፋዬ የሚባል የማያውቀው ሟች ልጅ እንደነበረው አራሳችሁ መርምራችሁ ድረሱበት። አዳም ስለተኮላ የሰጠው ድምዳሜ እንደሚከተለው ነው።

"**ተኮላ** በትክክል የአራዳ ልጅ አይደለም፡፡ **ተኮላ** የመጨረሻው የአዲስአባ እረኛ ነው::
አዲስአባ ግብርና እየሸሻት ሲሄድ የመጨረሻዋን ላም የጠበቀ፣ ከመጨረሻዋ በግ የተላፋ፣
በመጨረሻው አህያ የተረገጠ (ምናልባት አናቱ ላይ)
የመጨረሻውን እንኩቶ የበላ ነው፡፡

ከአንድ ቅጥ መረጃ አንድ ቅጥ መደምደሚያ ማግኘት የለመደ ባለጠፍጣፋ አንጎል ነው፡፡
ይሄ በከተማዋ ተወዳጅ የሆነ የመጨረሻው እረኛ በመጠጣት በመዳራትና እነዚህን ለማግኘት በመዋሸት ነው አራዳ የተባለው፡፡
የህብረተሰቡ መለኪያ እንዲህ ከሆነ ምን ያድርግ?

ፍቅር ግልጽነትን ለባብሶ ሲመጣ ሳር ጎዝጎዞ "ኖር' ማለቱ እንደከበደው፣ አለማድረጉም እንደጎዳው አልገባውም።" ገጽ 822

▪ አሁን ግን እዚህ ላይ የምንወያየው ስለ **ተኮላ** ፈስ ነው።
ሁሉን ቻዩ (In terms of literature) አዳም፣ ተኮላ የፈሳቸውን አምስት ፈሶች በሙዚቃ ኖታ (music notes) አስቀምጦልናል። አስቂኝ ነው።

ግን ከአስቂኝነቱ ባሻገር አዳም ለምን ተኮላ ፈስ ላይ በዚህ ልክ ትኩረት እንድናደርግ እንደፈለገ ለመረዳት ሞክሬያለሁ። ፈሱ አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት የፈሱ ድምፅ ለሱ ይሰማዋል ጠረኑ ግን ሌሎችን ያቀረናል እንጂ እሱን ምንም አይሸተውም። ይህ ገጽ 32 ላይ ያስተዋልነው የሆድ ህመምና የቀረና የፈስ ሽታ እየተባባሰ ሄዶ ገጽ 809 ላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዳበላሸበት ብሎም በገጽ 816 ላይ አባቱ ስፔሻሊስት ማየት እንዳለበት መከረውታል።

ከዚህ በኋላ ነው አዳም ቅርናታቸው የሚያንገሸግሽ ክፉ ክፉ ገጸ-ባሕሪያትን የሚያስተዋውቀን። በኔ አመለካከት የተኮላ ለራሱ የማይሸተው ሌላውን የሚበጠብጠው የፈስ ቅርናት ክፋታቸው ሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርሰውን የስነ-ልቦና ቀውስ የማይረዱ፣ አላማቸውን ለማሳካት በምንም እና በማንም ላይ የሚረማመዱ ሰዎችን ለማመልከት የገባ ነው።

የምቀኝነትን ጥግ ያሳየችን ሳላይሽን እራሳችሁ አንብባችሁ ድረሱባት። ነገር ግን የጎሰኛነትን ጥግ ስላሳየችን ፈያሜታ፣ ስሚገለማው የውስጥ ጠረኗ ትነሽ እናውራ።

▪ ፈያሜታ
የት ነው **ፈያሜታን** የምታውቋት?
ኦሮማይ ላይ?
ሰሜናዊት ቆንጆ ስትባል?
ትንሽ ነበልባል ስትባል?
ልዕልት ፈያሜታ ስትባል? ጣፋጭ ስትባል?
የባህር አማልክት፣ የቀይ ባሕር ርግብ ስትባል?
ዘፈኖቻችን ላይ፣ ቲያትሮቻችን ላይ Romanticise የምትደረገው **ፈያሜታ** ይህን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ አታገኟትም። እዚህ ላይ ያለችው **ፈያሜታ** አላማዋን ለማሳካት ከሀ እስካ ፐ የምታሴር እና ማንኛውንም አይነት ጭካኔያዊ ተግባር ከመፈጸም የማትመለስ ጎሰኛ/ዘረኛ ናት።

አዳም ምን እንዳደረገ የሚገባችሁ ገጾቹን እየገለጣችሁ በሄዳችሁ ቁጥር እየተጸየፋችኋት ስትሄዱ ነው።
Adam truly deconstructed the image of **ፈያሜታ** in the most brutal but magnificent way.
እስቲ ከፈያሜታ ታሪክ ውስጥ ከተጠቀሱት መሃል ጥቂት አንቀጾችን ላጋራችሁ።
"**ፈያሜታ** ዛሬ ድረስ ልቤን ተሸክማው የምትዞር ይመስለኛል፡፡ አነገተችው ቦርሳዋ ውስጥ ከጥግ ተቀምጧል፡፡ የሊፒስቲክ ዘንግ፣ ኮንዶም፣ የውስጥ ሱሪ፣ የተለያዩ ድርጅቶች። መታወቂያዎች፡

(የአዲስአባ ነጻ አውጪ ግንባር (አነግ)፣
የጉለሌነጻ አውጪ ግንባር (ጉነአግ)፣
የእሪ በከንቱ ነጻ አውጪ ግንባር(እበነግ)፣
የካዛንቺስ ነጻ አውጪ ግንባር (ካነግ)፣
የነፋስስልክነጻ አውጪ ግንባር (ነነግ)፣
የጉንጉን ነጻ አውጪ ግንባር(ጉነግ)፣
የጋርሶና የጆን ትራ ነፃ አውጪ ግንባር (ገጆትነግ)፣
ቀለም የተቀቡ ጥፍሮች ነፃ አውጪ ግንባር (ቀጥነግ)፣
የአውራጣት ነጻ አውጪ ግንባር (አነግ)፣
የጉበት ነጻ አውጪግንባር (ጉነግ)፣
የኩላሊትና የጣፊያ ነጻ አውጪ ግንባር(ኩከጣነግ)፣
የቀይ ደም ሴል አብዮታዊ ነጻ አውጪ ግንባር(ቀደሴአነአግ)፣
የፐላዝማ ነጻ አውጪ ግንባር (ፐነግ)

እና የማን እንደሆኑ የማይታወቁ ምሕፃሮች፡

የኦነኮ፣ የኮነግ፣ የቦነግ፣የጦነግ፣ የወነግ፣ የዶነግ፣ የጉነግ የሙነግ ግንባሮች)

የጥፍርቀለም፣ የማስቲካ ፓኮ፣ የባንክ ደብተር፣ ከነዚህም ጋር በሴቶች ነፃነት ስም የቀሰቀሰቻቸው ቂል ሴቶች በእምነት አስቀምጪልን ያሏት ከባሎቻቸው የደበቀችላቸው አንድ አራት የሚሆኑ ምንትሶቻቸው፡ የተገረዙና ያልተገረዙ፣ የጨገሩና ያልጨገሩ (ዮናስ ሲደበር ፋካካም የሚያደርጋቸው).........እዛ ከሁሉ ስር ከጥግ እርጥብ ልቤ ደም እንደ ወር አበባ ያዘንባል፡፡ አስኪ እንላፋሽ ብለን ፊያሜታን ዘቅዝቀን፣ ዕድሜው ገፍቶ ክብ መሆን የደከመው ሙልሙል ቂጧ ላይ በቀስታ ብንቸበችባት፣ በአፍዋ የሚወጡት ጃኖ የመሰሉ እርጥብ ብሮችና እንደ ምላሷ የሚያብለጨልጩ ተሙኖች ናቸው። ዘመኖቻችንም እንደ ሽረሪት ድር ይሆናሉ ይላል መዝሙረዳዊት.........ያው እንደ ሃጠራው ትብታብ........" ገፅ 326

"የቆንጆ እናቷ ውስጥ ልብስ ከደሃ ገበሬዎች ቆዳ የተሰፋ ነው፡፡
ቦብሊን ገበሩ የነዛ አራሾች ላብ ነው (አለነገር የሚፈስ መሰለ?)፡፡ የመኪናቸው ብረታ ብረት የዘር ማንዘራችን አጥንትነው፡፡ የሚንከባለልበት መንገድ ላይ ስንት የማይታይ ደም ፈሷል?

አስፋልት መሃል የፈረጠውን ሎሚ ፌሚ ቆሻሻ ብላ የናቀችው፣ ወሊሶ ያለ “መገርሳ" የተባለ ብላቴና፣ ወሎን ኮሚ ላለችው ቆንጂት ፍቅረኛው የወረወረላት ነው፡፡

ከመሃል ቆርጠሽ በታኑስሽ ያፈረጥሽበት፡፡ የመኪናሽን ጎማ ብትልሺው እማምላክን ለሚደማ ድድሽ ቤዛ እዛ ኣለ፡፡ አንዴ የሳምኳት አፍታ ያጋጠመኝ በከንፈሯ ትኩሳት የሞቀ ቀረፋ ነበር፡፡ ቀረፋው ከሸዋ ቆላ የተለቀመ ነው፡፡ ቅድመ አያቷ ዝሆን ሊገሉ ከባሕረ ነጋሽ ውደ አዳል በረሃ ሲወርዱ፣ ሞጆ ያደሩ ዕለት፣ ጠበል ያሞቃት ‘አቻምየለሽ‘ የምትባል ወይዘሮ ተራክበው እትዬ ሰንበትን ወለዱ፡፡ በሻይ አሟሙተሽ ሆድሽ ያስገባሽው ቀረፋ አቻምየለሽ አርጅተው ሲያልፉ የተቀበሩበት አምባ ላይ የበቀለ ነው፡፡ በርሞሌ አትፈልግም እብስ ይባል ይጥፋ እሜቴ አጥንት ላይ አብቧል ቀረፋ ብሎ ባላገር ዘፍኖላቸዋል፡ ፡ ይሄን ሁለቶ (እና ዘር ማንዘሮቹን) ዝተት እስኪሆን በጣጥቀን ‘መጀመሪያውኑ አልነበረም' ብለን እኔና አንቺ ደፍረነዋል፡፡ ቀረፋው እዚህ ጉልት ቅመም ተራ ዛሬም ይሸጣል፡፡ ንፋስስልክ ቀይ መሬት እትዬ ላስታ መደብ ላይ ተዘርግቶ፣ እሱን አቧራ የተነሰነሰበትን “ሲጣፍጥ” እያለ ያልጠጣ ማነው?" 327-328

"የአድጊ ባህርይ ይሄ ነውና እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ አድጊ ወዳጆቹ ላይ በወሬም በድርጊትም ያድማል፡፡ በነጠላ በነጠላ እየሸራረፍን እናጠፋዋለን፡፡ ለሌላ መከራ እንደቀጠርነው አይገባውም። እኛ እንደ ደርግ በአንድ ዓመት ቀይ ሽብር ሳይሆን ሳብ ረገብ በሚል የአርባ ዓመት ቃሪያ ጥፊ ነው ከምድረ ገፅ የምናጠፋው::

ከዚያ እግዜርን ያማርራሉ (እግዜርን ቢያማረሩ ሰላማዊ ሰልፍ አይወጡበት)፣ ራሳቸውን ያማርራሉ (ራሳቸው ላይ ሰላማዊ ሰልፍ አይወጡ)፡፡ የሚቀራቸው አማራጭ _ ዞሮባቸው ደጀሰላም መዘፍዘፍ ነው፡፡ እኛ ደጀሰላሙን እንዲያስፋፉ መንገድ መክፈትና ብልጣ ብልጥ ደብተራዎችንእንዲጠብቁት ማድረግ ነው፡፡ ከብት ምን ይደረጋል? ይጠበቃል እንጂ፡፡ ሰው ተሻሽሎ ሃይማኖተኛ የሆነ ይመስለዋል፡፡ እዛ ደርሶ ሲመለስ ቤቱ፣ መሬቱ፣ ሚስቱና ምንትሱ የሉም፡፡" ገጽ 672

"***ፊያሜታ*** የሰገነቱን ብረት ተደግፋ የጨለመውን የአዲስአባ የሲሶ ሲሶ ዓለም ወደ ታች ወደ ላይና ወደፊት ለፊቷ እያየች ቆማለች፡፡

ከአገሯ (ባትልም) ወደ ሃያ አመታት ያህል እርቃ ስለኖረች አዲስአባ ከገባች ጀምሮ እስከአሁን መናገር የሚቀናት በእንግሊዝኛ ነው:: ዘመኑና የማሴር ፍቅር አስገድዷት እንጂ ዐማርኛ መናገር ትጠላለች፡፡

*ዐማርኛ አክሱማዊ ቋንቋ ነበር ቢሏትም አይዋጥላትም፡፡ የአክናቶንና የጡት-እንካ-አሞን ቋንቋ እንደነበር አታውቅም፡፡ ሁለተኛዋ ህንደኬ ቅንዳቅስ ከማኬዶናዊው እስክንድር ጋር ተኝታ ያቃሰተችው በዐማርኛ እንደነበር አይገባትም፡፡ ቢገባትም፣ ከዘሯ ሳይሆን ከዛሬ ዘመን ጋር ፍቅር ይዟታል፡፡ምክንያቱም ትንሽ ናት፡፡ እነዚህ መረጃዎች ቢሳቷትም ግን የአፍሪካ ቀንድ የተባለው ሁሉ ለአመለካከቷ ባሪያ ነው፡፡ በዚህ የሆነ ኩራት ይሰማታል፡፡ ኩራቷም ከፀባይዋ ይነበባል፡፡ ከአቋቋምዋ*

ይተነበያል፡፡ የሌላ ባርያ ብትሆንም 100 ሚሊዮን የሚደርስ ባርያ አላት፡፡ ከዚህ የበለጠ ማሸነፍ አለ? በአሜሪካኛ ዊነር የሚሉት? ባሮቿ ባይወዷትም ይፈሯታል፡፡ሕይወት እኮ ይሄ ነው፡ መፍራትና መፈራት፡፡ ሌላው ገብስ ነው፡፡" ገጽ 877
"ቤት ስራ እኮ ያልቃል፡፡ ደሞ መሪዬን ማሽሟጠጥህ ነው? ቆራጥ መሪ ነው ያለኝ: ይሄ ቤት ስራ አይደለም፡፡

እኛ ከሌለንባት እዚህች ሀገር ላይ ማንም አይኖራትም፡፡ ይህቺን አገር ለመምራት አንጎል ያስፈልጋል፡፡ አገሬን እኮ መከላከል አለብኝ፡፡ አይደለም እንዴ? እኔ ቀጥ ብዬ እንድጓዝ ሰማንያ ሚሊዮን አህያ በጠማማ መንገድ መሄድ አለበት።
ለማጣመም እንዲመች እዚህ አብረኸው ትሆናለህ፡፡

ሊዘፍን ሲል ቴፑን ታበላሻለህ፡፡

ማን አበላሸብኝ? ሲል አንዱን የራሱን ሰው ትጠቁመዋለህ፡፡መጀመሪያውኑ የእኛ ነገር እንዲል። ዓለም ይተባበረናል፡፡ እስኪ የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑ ስትቸገር የሚደርሱላት አገሮች ዝርዝርንገረኝ፡፡ አንድ ጥራልኝ፡፡" ገጽ 890

"በትክክል ግን ልቧ ውስጥ ያሉት ባሏና ልጆቿ አይደሉም፡፡ ፀጋም አይደለም፡ ኤርትራን በመውደድ ኢትዮጵያን በመጥላት ሁለት ስሜቶች ከአንዱ ወደ አንዱ እየነጠረች የምትጋጭበት ሃላቧነው:: ጥልቅ እምነትም የሆነባት በሌላ ዓይነት ፍቅርባ ለመበረዙ ነው:: እዚህች ክፍል ፀጋን ብትወደውም፣በየሄደችበት ቢናፍቃትም፣ ሳያቋርጥ በልቧ የተሰገሰገው ግን የቅኝ ገዡዎች ወጥመድ ነው፡፡ የዛን ብልት ግድግዳው ቧጦ ከያዘ መላቀቂያ የለውም: ሙሶሎኒ ሐውልት ቢኖረው ሐውልቱ ነፍስ ቢኖረው ሐውልቱ ፊያሜታ የምትሰራውን ስራ ቢያይ የሐውልቱ ዳሌ ቢነቃነቅ እናም ይሄ ሐውልት አንደበት ቢኖረው 'የአፍሪካን ቀንድ እስከዛሬ እያደረኳት ነው' ብሎመናገሩ አይቀርም፡፡" ገጽ 891

▪ እስቲ ደሞ ስለ **ቤላ** አሳዳጊ **ተስፋዬ** እናውራ
**የተስፋዬ** የበሰበሰ ማንነት የተገለጠው አሳድጋለው ብሎ ወስዶ የዘላለም ስብራት ባደረሰባት **ቤላ** ላይ ነው።
ሰዎች ግም ወይም ግማታም ብለው ሲሳደቡ ስሰማ በሃፍረት አሸማቀቃለሁ። ነገር ግን ተስፋዬ ከዛም በላይ ይገባዋል። እዚህ ላይ ስለ አዳም የምለው ነገር አለ። ከዚህ ስር ያሉትን አራት አንቀጾች ስታነቡ ይህን የመሰለ ጭካኔ የተገለጸበትን የቋንቋ ውበት አለማድነቅ ይከብዳል።

(How is it possible for something so terrifying to be described with such breathtaking aesthetic beauty? It almost feels wrong to appreciate the elegance of how such a harrowing incident is portrayed – but that's the power of Adam's pen)

አንዲት ሴት አየተደፈረች የሚያሳይ ጽሑፍ እያነበብን፣ ስቃይዋ ልባችንን ሰንጥቆ እያደማን ግን ደሞ በመሃል ቆም ብለን በአጻጻፉ ስልት ከተደመምን ጸሐፊው ስራውን በሚገባ ሰርቷል።

"ዕድሜዬ አስራ አራት እያለ አንድ እሁድ ጠዋት አሳዳጊዬ **ተስፋዬ** መታጠቢያ ቤት እንድመጣ ጠርቶኝ እዛም ገብቼ ገላዬን እሺኝ ብሎ አረፋ የደፈቀ እርጥብ ስፖንጅ ሰጠኝ።

ሌላ ጊዜ ገንዳ ውስጥ እንደ ተጋደመ በመጋረጃ ተጠልዬ ፎጣ አቀብዬዋለሁ፣ አሙለጭልጮት የወደቀ ሳሙና አንስቼ ሰጥቼዋለሁ፣ ነጠላ ጫማ አቀብዬዋለሁ፡፡

ያን ቅዳሜ ጀርባዬን እሺኝ ብሎ መታጠቢያ ቤት ስገባ መጋረጃውን እስከመጨረሻው ገልጦ ገንዳ ውሃ ውስጥ እስከ ዕንብርቱ ሰምጦ ፈገግ ብሎ አየኝ፡፡ የሚያስቅ ነገር አልነበረምና አልሣቅሁም፡፡
በእጁ የያዘውን ስፖንጅ አቀበለኝና ወደ ጀርባው አሳየኝ፡፡ ኮስተር ብዬ ጀርባውን ማሸት ስጀምር ዞር ብሎ እጄን ጎትቶ ወደ ፊት አስጎነበሰኝና 'ነገሮዬውን' አስነካኝ፡፡ አውሬ እንደቧጨረኝ ሁሉ ጮኬ ሳሙናው እጄን ሙልጭልጭ ስላደረገው በቀላሉ ነጥቄው ማምለጥ ቻልኩ፡፡

ቀኝ እጂ እባብ የነካኝ መስሎኝ ሃያ ጊዜ ያህል ታጠብኩ፡፡ ጣቶቼ ላይ ተጣብቆ እንደቀረ ሁሉ ሺህ ጊዜ እጄን አርገበገብኩ፡፡ ንክኪውን ባሰብኩ ቁጥር ደሞ በእንትኑ ልስላሴ እየተገረምኩ ሁለመናዬ ይንቀጠቀጣል፤ የሁሉ ነገር እንግዳነት ኣእምሮዬን ይነክሰኝና በፍርሃት ዐይኖቼ እንባ ያቀራሉ፡፡

ያን ዕለት ፈርቼና ጮኼ ቢተወኝም **ተስፋዬ** አለቀቀኝም፡፡ የሚጠጣ ውሃ ሳቀብለው ጣቶቼን ከነብርጭቆዎቹ ጋር ጨበጥ አድርጎ ሲለቀኝ፣ እንግዳ በሆነ መልክ ከፍ ዝቅ አድርጎ ሲያየኝ፣ በፍርሃት እሸሸው ጀመር፡፡ ገና ሲጠራኝ ሁለመናዬ ይርዳል፡፡ ሁሌ የማየው በደንብ የማውቃቸው ዐይኖቹ ናቸው፣ ግን ከዚያን ቀን ጀምሮ የተለየ ሆነብኝ፡፡ ከዛ ወደ እዚህ አለዋወጡ የሚያስፈራ ነገር ነበረው፡፡ ዐይን ይለወጣል ይባላል እንዲህ ነው:: ማምለጥ ግን አይቻልም፡፡ ወዴት አመልጣለሁ? አንድ ቀን ማታ እተኛሁበት ያዘኝ፡ ሚስቱ የለችም፡፡ ማንም የለም፡፡ ባለጌ ነውና አያስፈራም አያስፈራም አይዞሽ ቤልዬ ቤላ እያለ ደፈረኝ (ለምን የምወደውን ስሜን ጠራ? ለምን መአዚ መአዛ ምናምን አይልም ነበር?)፡ ጅብ ካለፈ ውሻ ጮኽ ነገር ላይ ዝርዝርና ምርምር ምን ይጠቅማል ግን? ገጽ 81

"ለምን ስለዚህ ኦፔራ ለይቼ አነሳሁ? **ተስፋዬ** የደፈረኝ ይሄን ኦፔራ እየሰማሁ ነው:: ወይም ድንግል መሆኔ ሲያበቃ በአንሶላ ተጠቅልዬ ተስፋዬ ውስጥ ሱሪውን እየለበሰ፣ የእኔም እናት በራስ ምታት እየዞረ የኦፔራው ዜማ ከዋናው ቤት ወደ ተኛሁበት ሰርቪስ ቤት በሚያሳዝን መልክ እየፈሰሰ እሰማው ነበር። ተስፋዬ የልቡን አድርሶ ትቶኝ ሲወጣም ከኦፔራው የቀለበውን፡ The past is now another land እያለ ነበር፡፡ ነው ግን? የሚረሳን የመሰለን የቆየው ነገር በራሱም ይሁን በራሳችን ግፊት ዛሬ እንደሆነ ሁሉ ገዝፎ ይታየን የለ? እዚህ በአይናችን ባናየውም…… ባንዳስሰውም አውጥቶ ባያሰማንም………በአካል ባይኖርም ድምጹን አእምሮአችን ውስጥ የልጅነታችን ሰናፍጭ ትውስታ ዳሸንን አክሎ ይመጣል፡፡ በቻልታ የሣቅንበት ጉድ` ጉድ' ዛሬ ሰንጢ ሆኖ የእንባ ቀረጢታችንን ይቀዳል፡፡ ስራቀቅ አይደለም፡፡" ገጽ 82

"ከተስፋዬ ጋር የምንግባባበት ቅፅል ነበረን፣ እሱ እራሱ የፈጠራት ኮድ ነገር፡፡ እላዬ ላይ ሆኖ እያለከለከ (ሲጀምር የሚያስፈራኝ እየቆየ ግን የመሰጠኝ) እንደ ፎርሚያጆ አሲያጎ የምትጣፍጪ ይለኝ ነበር፡፡ ዛሬ ድረስ ግራ ጆሮዬ ላይ ትንፋሹ ይሰማኛል (ለምን ሁልጊዜ ወደ ግራ ትከሻዬ ብቻ እንደሚያጎነብስ አይገባኝም)፡፡ የሚያደርገውን አድርጎ አንሶላ አልብሶኝ ትቶኝ ከክፍሌ ሲወጣ እላዩ ላይ ተጣብቆ የሚቀረው የወንድነቱ ጠረን ብቻ አልነበረም፡፡ ይሄም ቃል ነው፡ ፎርማጆ አሲያጎ፡ አልወድም ፎርማጆ:: ቢሉኝ ቢሉኝ እስከዛሬ ይሄን ኣይብ አለመድኩም፡፡ ለምን አትበይም በእናትሽ ብዬ ምናምን ካሉኝ ላም እጠላለሁ እላቸዋለሁ፡፡ ፋኒ" ነኝ አደለ? ታዲያ ተስፍሽ እኔን ሲፈልገኝ ልጆቹ ቢኖሩም………'ዛሬ አሲያጎ ቺዝ የለም? አለቀ እንዴ?' ብሎ ያየኛል፡፡ ትርጉሙ ዛሬ እናደርጋለን ጠብቂኝ ነው:: " ገጽ 83

▪ የተስፋዬ ቅርናት በቤላ ላይ ያደረሰው የስነ-ልቦና ቀውስ በቀላሉ የሚድን አየደለም። የሕይወቷን ጉዞ አዳም በዚህ መልኩ ገልጾታል።

"በመጀመሪያ ከሰዎች ፊት ሞገስ እንዳላገኝ ያደረገኝ መልኬ አለ፡፡ የሚታይ ነገር የላትም ይባላል፡፡ እንደዛ ዐይነት ልጃገረዶች አለን በዓለም ዙሪያ የሚታይ ነገር የሌለን፡፡ ቢኖረን እንኳን እንዳንታይ ይመኛሉና በአጠቃላይ አባባልና ስያሜ የማንታይ ያደርጉናል፡፡ የሚገርመኝ ግን ወንዶች ያቺን ነገር ሲፈልጉና ሲያሰኛቸው የሆነ ነገራችን ይከሰትላቸዋል፡፡ .....
ሁለተኛ መልከጥፉን በፖለቲካ ይደግፉ' ሲባል አዳሜ ላትሰሚ ትችያለሽ፡፡ ግን ይባላል፡፡ በሁዋላ የ66 አብዮት ተነስቶ 'ተሳተፊ' ብለው ሲመለምሉኝ በፖለቲካ ቲያትር ውስጥ ፉንጋነቴ ጠፋ፡፡ ሊያቅፉኝ፣ ሊስሙኝና ሊወዳጁኝ ያልተመኙኝ እንድሞትላቸው ፈለጉ፡፡

ወጊ ይረሳል፡፡ ቤላ አትረሳም፡፡
እንደ ፊያሜታና በቅርብ እንደማውቃቸው ሴቶች ልጆች የምኮራባቸው ተጨባጭ አባትና እናት የሉኝም፡፡ የታሉ ወላጆችሽ? ቢሉኝ ደህና ፎቶ እንኩዋን ማሳየት አልችልም፡፡
መልማዮቼና መሰሎቻቸው ከሚኖሩበት ሃሳባዊ ሀገር ከጠርዙ ላይ የምመላለስ ባለጌ ስርዓትና አጃቢዎቻቸው የፈጠሩኝ ዕድለ-ቢስ ነበርኩ፡፡

ስፈለግ የምጠራ፣
ሲፈልጉ የሚረሱኝ (ግማሽ ዕድለ ቢስነት አለ?)፡፡

በጥጋበኞች የተገፋሁ እንደ ገና ዕድሜዬ ከፍ ሲል ጥጋበኞች እንዲገነጠሉ አደጋ ቀማሽ የሆንኩ፡፡ ይሄም ይገባኛል፡፡ 'ጠላታችሁ ኢትዮጵያ ናት' እየተባለ እየተነገረን የምናድግ ስለሆነ ረቂቅ የሆነው የውስጥ ባርነት አይገባንም፡፡ ከላይ የተሽቀረቀርንባቸውን የሚያብረቀርቁ ቀሚሶችና "ቀሚሳት" በትንሹ እንኩዋን ገልበው ቢያዩአቸው ገበራቸው አደፍ የነካው ነው፡፡" ገጽ 85

"**ተስፋዬ** ቶሎ ለመብሰሌ ትልቅ ግብአት ነበር፡፡ እኔን ከሕግ ይሁን ከስነምግባር ውጭ እየተኛኝ ታላቅ ፍትህ ፈላጊ እንደሆነ ሰው ኢትዮጵያ እሱን ኤርትራዊውን እንደምትጨቁን በንቀት ስሟን እየጠራ እንደ መጥፎ ሴት ሲሰድባት በሆዴ እስቃለሁ፡፡ የፈለገውን ዐይነት ሰው ቢሆን፡ ቀማኛ፣ ባለጌ፣ አረመኔ ብቻ ኢትዮጵያን የሚያጥላላ ፍልስፍና ካየበት ተስፋዬ ወዳጁ ነው:: የስነምግባሩ መለኪያው ይሄ ነበር፡፡ ወደ አደባባይ ሲወጣ ልቡን ቤቱ አስቀምጦ አፉን ሰፋ ያደርጋል፡፡ ታዲያ ያለሁበትን፣ ያደኩበትን፣ ያበላኝና ጡጦዬን የሞላልኝን ማስደሰት አለብኝና እንደ ሃሳቡ እሆናለሁ፡፡

በአንፃሩ ደሞ ምቾት የሰጠችውን ይህቺን ሀገር አንካሳ እንግሊዝኛ እየተናገረ ሊገነጥል ከፈለገ፣ እሱ ተስፋዬ ምቾት ቢሰጥኝም ለምን በእሱ ጥበብ አልሸውደውም? ይሄ ቢያንስ የእሱን ስልት የመቅዳት ችሎታ ይጠይቃል:: የሆነልኝም እሱን የመሳሰሉት ስለፈጠሩኝ ነው:: በማስመሰል ስላደኩ ነው:: ያሳደጉኝ እንደፈጠሩኝ ይረሱታል፡፡ ሞዛዛ ብለው ሲጠሩኝ በሆዴ እስቃለሁ፡፡ የሆዴ ሣቅ ሚስጢሬ፣ ሚስጢሬም ነጻነቴ ነበር። ከዚህ የሕይወቴ ፍሰት የተማርኩት ቁልፍ ዕውቀት ሁለትነት ሃይሌ እንደሆነ ነው፡፡ ግን ነጻነትን ተደብቆ መኖር የድብርቶች ድብርት አይደለ?" ገጽ 86

"በልጅነት መውለድ ሴትን ይጎዳል፡፡ ከትዳር ውጭ ማለቴ ነው። ባለጌ፣ አብሻቂና ወግ አጥባቂ ሰዎች መሃል መደቀል ደሞ መከራውን ያበዛዋል፡፡ ከማን እንደወለድኩ አደባባይ አለመውጣቱ ዋናው ነው:: ከማን እንዳረገዝች እንኩዋን አታውቅም ጉድ ጉድ እየተባልኩ ተስፋዬ ራሱም ተሳታፊ እንዳልሆነ በእርግዝናዋ ነገር የለሁበትም ለማለት ተደምሮ እየሰደበኝ ያከሳኝ ያቆረቆዘኝ ጊዜ አለፈ፡፡ እንኩዋን ሆኖ ይቅርና ሳይሆን ሊሰይሙን፣ ቅጽል ስም ሊሰጡን ይቸኩሉ የለም?

የተስፋዬ ዋናው ስድብ ወዲ ሸርሙጣ ነው:: እንግዲህ እናቴ ሸርሙጣ፣ እኔ ሸርሙጣ፣ ልጄም ወዲ ሸርሙጣ፡፡ ያሳዝናልም ያሳስባልም፡፡ ስማርት ስለሆንኩ ነው የሚያሳስበኝ፡፡ የሚያሳዝነኝ ደሞ ልብ ስላለኝ ነው:: መውለዴ የጠቀመኝ ነገር ቢኖር ተስፋዬ ስለፈራ ወደ ዐልጋዬ አለመምጣቱ ነው፡፡ ደግሜ የምወልድበት ስለመሰለው አይጠጋኝም ነበር (ወይም አልቁበት ይሆናል)፡፡" ገጽ 89

"የማሽሞነሙነው የምሽቱ ገላዬ ባዕድ ሆነብኝ:: ፀጉሬ አልታሰረም። እንደማነብ ሁሉ መፅሐፍ አነሳለሁ፣ ከዛ አንድ ሁለት ገጽ ገልጬ አይና እጥለዋለሁ፡፡ ባዶ አየር ላይ አፈጣለሁ፡ የማየው ግን ወደ ውስጤ ነው::

ውስጤ ባዶ ነው::
ፊያሜታን ጠላሁዋት፡፡ ራሴኑ የሚሸውድ ዘመን ጎትቼ እንዳመጣሁ አልገባኝም፡፡ ፊያሜታ ጎድታኛለች? ባሌን አላወጣች፣ ፍቅረኛዬን አልቀማችኝ፡፡
ያሳለፍኩት የብልጠት ዘመን በእርግጥ የብልጠት አልነበረም፡፡ ቀን ጠብቆ በራሱ ሎጂክ ሁሉ ነገር እየተናደ በላዬ ላይ የመጣ መሰለኝ፡ ያውም በፍጥነት፡ ዕውን የሆነ ቲያትር ነው የኖርኩት? ማልቀስ መጀመሬን ልብ አልኩ:: ባልንሰቀሰቅም ዕንባ ይወርደኛል፡፡ የምሰብረው የማንኮታኩተው ነገር ፈለኩ፡፡ ማድረግ ግን አልቻልኩም……..

እስከ ማታው አምስት ሰዓት በትግል አርዕስት ስር ተቦርቡሮ ስላለቀው ብልጥ ስላሰኘኝ ሕይወቴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እያለፍኩ እያለፍኩ አሰብኩ፡፡ ራሱም ያሰበኝ ይመስላል። ሃሳቦች ስለ አሳቢያቸው ያስባሉ? አንዳንዴ ይመስላል፣ ተጠንተው የተዘጋጁ ርዕዮተ አለሞች ቁጭ ብለው የደደብን ነፍስ ለመውረር የሚጠብቁ ምናምን ናቸው:: ሊነጋ ሲል እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ ዘካርያስ እኩለ ሌሊት ቤት ሊተኛ ገብቶ እኩለ ቀን ላይ ወደ ውጭ ሲሄድ በር ሲዘጋ ባነንኩ፡፡ ጮክ ብዬ ተጣራሁ፡ «ዜድ!» ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ከውጭ ሲከፈት ሰማሁ፡፡ ቅር ብሎት እንደተመለሰ አልጠፋኝም፡፡ መኝታ ቤቴ በር ሳይገባ ቆሞ፡ «ለብሰሻል?» አለ «ግባ የእኔ ጌታ» በጀርባዬ ዐልጋ ላይ ሆኜ ሳየው ልክ እንደ አባቱ ረኸም መሰለኝ፡፡ በዝምታ አየሁት:: ከሆዴ ሲቃ ሲመጣ ይሰማኛል፡፡

እናትነቴን በጠማማ ፖለቲካ ነፍጌዋለሁ፡፡ ብዙ ነገሮች እንደነፈኩት አይገባውም፡፡ ልጆች የእናቶችን ስህተት የገብጋባነት አድርገው አይወስዱትም:: ታስቦላቸው ይመስላቸዋል፡፡ ንፍገት እንደማሰብ ይተረጎማል፡፡ ይሄ አንጀት ይበላል፡፡" ገጽ 881-852

■ እዚህ መፅሐፍ ላይ **ቤላ** የምታደርጋቸው ጎሰኝነትን የሚያራምዱ ጭካኔ የተሞላባቸው አፀያፊ ክስተቶች ቢኖሩም አንባቢው በቀላሉ ይቅር ከሚላቸው ገጸ-ባሕሪ አንዷ ናት። ልጅነቷ በመቀማቱ እናትነቷም ተቀምቷል። ባዶነቷ በተስፋዬ ቅርናት መታወዱ ያስለቅሳል። ተስፋዬ የፈፀመው አመፅ ቤላ ላይ ብቻ ሳይሆን ልጇና ማህበረሰቡም ላይ ነው።